# ከገማ ዕንቁላል ጫጩት አይጠበቅም!

አሥራደው (ከፈረንሳይ)

ማሳሰቢያ:

ሃገራዊ ምሳሌዎችን (ጥቅሶችን) እንደመጠቀሜ፤ ጥቅሶቹ የተጠቀሱበትን ሃሳብ ከሰሩ ካላሰፈርኩ: የትኛው ምሳሌ: ለየትኛው ሃሳብ: ገላጭ መሆኑን ለአንባቢ ግር እንዳይል በማሰብ ከጥቅሱ በመቀጠል ወዲያው ሃሳቡን አስፍሬያለሁ::
በተረፈ ሃገር በቀል ምሳሌዎች (ጥቅሶች): ውስጠ ወይራነት ስለተካኑ: ከነጫቹ ቋንቋ በበለጠ የገላጭነት ባህሪይ ስላላቸው: ጸሐፍት ይሀን የአገር ሃብት: ያለገደብ በመጠቀም: ለተተኪው ትውልድ እንዲያስተላልፉ አደራዬ የበረታ ነው::
የነዚህ ምሳሌዎች (ጥቅሶች) ባለቤት ለሆነው: የኢትዮጵያ ሕዝብ ምስጋና ይግባው::

መንደርደሪያ

1. « ማሰብ ክልክል ነው!

መጻፍ ክልክል ነው!

መናገር ክልክል ነው!

መሰብሰብ ክልክል ነው!

ሰላማዊ ሰልፍ ማድረግ ክልክል ነው!

ነገር ግን፤

መራብና መከልከል ብቻ በኢትዮጵያ አልተከለከሉም» !!

አቶ መለሰ ዜናዊ ለኢትዮጵያ ሕዝብ አመጣሁለት የሚሉት ዲሞክራሲ::

2. « ከአማሩ አይቀር ቂጢጥ ከገሙ አይቀር ብሽቅጥ»

ለወይዘሮ አረጋሽ አዳነ እና ለአቶ ሰዬ አብርሃ ፤

«አረና ትግራይ»= የትግራይ ደጀን (በትርጉም ለተባበሩኝ የትግሪኛ ተናጋሪ ወንድሞቼና እህቶቼ ምስጋና ይድረሳቸው ) ትርጉሙ የትግራይ ደጀን ከሆነ: እነ አቶ ሰዬና ተከታዮቻቸው: አሁንም በጎሳ አንቀልባ እንደታዘሉ በኢትዮጵያ ሃብት እሹሩሩ የሚባሉበት ጉዳዩ ምንድነው? ትንሽና ጠባብ ሆኖ ከመሞት: አድጎ ተመንድጎ መሞት ጸጋ ነው: ታዲያ «አረና ትግራይ» የትግራይ ደጀን ብቻ ከመሆን ይልቅ: «አረና ኢትዮጵያ» «የኢትዮጵያውያን ሁሉ ደጀን» መባሉንና ትልቅና ሰፊ: ሁሉን አቀፍ: መሆኑን ለምን ጠሉት?

ዛሬ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ፡ የጎሳ ብርድልብሳቸውን እንደተከናናቡ ፡ ሌላው ወገናቸውን ፡ በድሪቷቸው ቀዳዳ እያሾለቁ የሚያዩ መሪዎችን አይሻም ::
እነ አቶ ሰዬና ተከታዮቻቸው ግልጽ ሊሆኑ ይገባል ኢትዮጵያዊነቱ ለምን አስፈራቸው ?

« አልሰሜን ሁለቴ ቅበረው » ይላል ያገሬ ሰው ፡ በነ አቶ መልስ ዜናዊ የተጀመረው ወያኔ ምዕራፍ 1 ስለተጠናቀቀና የሕዝብ ተቃውሞ ስለበዛበት፤ ወያኔ ምዕራፍ 2ን ደግሞ በነሰዬና መሰሎቻቸው ፡ ለመቀጠል ይሆን? ላለመሆኑስ ምን ዋስትና አለን ? ወያኔ የሠላሙን በርና መስኮት ፡ ክርችም አድርጎ ዘግቶ ባለበት በአሁኑ ወቅት፤ አቶ ሰዬ ፡ ወያኔ የዲሞክራሲ ፍርፋሪ እንዲመጸውተን ፡ ለምኑት ተለማመጡት እንጂ አትጋፉት ነው የሚሉን :: ወያኔ በበኩሉ ፡ በሱ ልክ ተከርክሞና ተለክቶ ፡ የተሰፋ የዲሞክራሲ ትብቆ አልብሶ ፡ አደንቁሮና አሰርቦ፤ በዝምታ ባሕር ውስጥ ዘፍቄ ነው የምገዛችሁ ይለናል ::
እንግዲህ ጎበዝ .....

ሌላው ፡ ወያኔ የዕርዳታ እህል ሸጦ ለጦር መግዣ የሚዋሉን ምሥጢር ፡ በማንኪያ እየቆነጠርን እንጂ ፡ በጭልፋ ለኢትዮጵያ ሕዝብ አንናገርም ማለታቸውስ ወያኔ (ህውሃት) እንዳይቀየም ወይስ ከመጋረጃ በስተጀርባ ሌላ አጀንዳ?!

## 3. « ከሾክ የተጠጋ ቁልቋል ዘወትር ሲያለቅስ ይኖራል »

ለመኢአድ፤

ወያኔ እያዋከበን ፤ አባሎቻችንን እያስፈራራና እያሰረ ነው የሚሉን « በነጮች ኩርኩም » ተለውሶ ፡ በወያኔ ጓዳ ተደግሶ « ሰጥቶ የመቀበሉን የሰነ ዝም በል ! ስምምነት » መፈረማቸውን ረስተውት ነው ?

## 4. « ሁለት ፈሳሞች ሲገናኙ ፡ ሸታዬ፤ ሸታዬ፤ ይባባላሉ »

ለአቶ መለስ ዜናዊና ፡ ለአቶ ኢሳያስ አፈወርቂ ::

ሰሞኑን አቶ መለስ ዜናዊ ፡ ከመሰላቸው የኤርትራ መሪ ፡ አቶ ኢሳያስ አፈወርቂ ጋር በየትኛውም ቦታ ፡ በማንኛውም ጊዜ ለመነጋገር ያደረጉት ጥሪ ነው::

ኤርትራ ፡ ከኢትዮጵያ ተገነጠልኩ ብላ ፡ ባወጀችበት ወቅት ፡ አቶ መለስ ዜናዊ በአሥመራ ተገኝተው ፡ ያደረጉትን ንግግር ስናስታውስ « ሁለታችሁም ከጀርባችሁ ያለው ጠላት የኢትዮጵያ ሕዝብ እንደ ነበር ነግረውናል» ዛሬ የኢትዮጵያ ሕዝብ ወያኔን አሸቀንጥሮ ለመጣል ቆርጦ ሲነሳ የድረሱልኝ ጥሪ መሆኑ ነው ?

## 5. « የምለውን እንጂ የማደርገውን አትዩ »

ለፓስተር ዳናኤል

የብርቱካንን በወህኒ ቤት መንገላታት: (እንደሳቸው ተልዕኮ አለመንገላታት) ለማሳየት: በቃሊቲ ወህኒ ቤት የሰሩትን ትያትር ስንመለከት: የሃይማኖት ሰዎች እንኳን: ለሆዳቸው እንጂ: ለሕሊናቸው የማይገዙበት: ዘመን ላይ ደርሰናል ያሳዝናል ::

## 6. « የሳጨን ልጅ ቅማል በሳት »

ለኢትዮጵያ፤ተማሪዎች

መሬት ላራሹ በማለት ሰንት ወጣት ሕይወቱን ለአርሶ አደር ወገኑ እንዳልሰዋ ዛሬ ወያኔ፤

መሬት ለድንበር ዘለል ከበርቴ: በመቸብቸብ፤ ገበሬውን ለጉልተኝነትና ለሁለተኛ ዜግነት: በመዳረግ በፈሰሰው የሃቀኛ ልጆች ደም ይሳለቃል ::

ተማሪው « መሬት ላራሹ ! » በሚል መፈክሩ ባደረገው ትግል የዋጀውን የመሬ ባለቤትነት ድል : ወያኔ ዛሬ ከሕዝብ ፈቃድና ፍላጎት ውጪ: ሻጭና ለዋጭ ፤ ሰጪና ነሺ፤ ወይም አከራይ : መሆን አይችልም::

ከወያኔ የተረፈን ከትውልድ ትውልድ የሚተላለፍ የብድር ዕዳ፤ በድንበር ዘለል ከበርቴ ቆሻሻ የተሞላች ኢትዮጵያ፤ ብዙዎች የሚራቡባት፤ ጥቂት ዘመነኞች የሚንደላቀቁባት፤ ገሃነም አገር ስለሆነ ካንተ በፊት የነበሩ ወጣቶች ሕይወታቸውን ለለገሱለት በጎ ዓላማ ክንድህን አንሳ! ወጣትነትህ ለአገርህ ደጀንና መከታ : ለራስህ መከበሪያ : እንጂ ለወያኔ የመገበሪያ ቁና መሆን የለበትም ::

## 7. « ዘወትር ከመፍሳት አንዴ ማራት !»

ለኢትዮጵያ ሕዝብ

ዘወትር ተረግጦ ላለመገዛትና ከወያኔ ዘረኛ፤ ከፋፋይና ዘራፊ አገዛዝ ለመገላገል በአንዲት ኢትዮጵያ ጥላ ስር ለጋራ ጥቅምህና ክብርህ ስትል በአንድላይ አብረህ ተነሳ !!

## 8. “The Original Sin is to Limit IS Don’t” !!

*ለአቶ መለስ ዜናዊ*

*የአበሻ ፈረንጅ በመሆን: በራሳቸው ቋንቋ የሚያፍሩ፤ በፈረንጅ ቋንቋ የሚወጠሩ፤ በመሆናቸው እንጂ: ለዚህ ምትክ የሚሆን የአማርኛ ምሳሌ አጥቼ አይደለም::*

*መቼም አቶ መለስ: የአማርኛ ቋንቋን የሚጠቀሙት: የኢትዮጵያን ሕዝብ ለማስፈራሪያ፤ ለመዝለፊያና ለመስደቢያ: በጥቅሉ በሸውራራ አጠቃቀም ሲሆን፤ ትግሪኛን ደግሞ: ከቀሪው የኢትዮጵያ ሕዝብ: የሚደብቁት ምሥጢር ሲኖራቸው ነው፤ እንግሊዘኛውን ደግሞ: አንድም ለመመጻደቂያ፤ ሁለትም ለነጮች አገልጋይነታቸውን ለማብሰር ሲሆን::*

*ሰሞኑን ደግሞ ፈረንሳይኛውን:* “ሴ ላ ቪ!” (c’est la vie!) *በሚል ጀምረዋል:: ሲመነዘር “ሕይወት ነው!” መሆኑ ነው ኪስ ካልቀደደ: በስተቀር:: በኮፐን ሃገን ስብሰባ ላይ: ከፈረንሳዩ መሪ: ሳርኮዚ የተዋሷት መሆኑን አልጠራጠርም:: እሱም ብዙ ጊዜ ሲጠቀምባት እንሰማለን: እሱም እዚህ እንደሳቸው በመጠላቱ: የፈረንሳይ ሕዝብ: በቅርቡ ባረደገው ምርጫ: በዲሞክራሲ በትር እንደነረተው ማን በነገራቸው? እዚህ ሃሳብ መገደብ፤ ማስፈራራት፤ ማፈን፤ ተናገርክ ወይም ጻፍክ ብሎ ማሰር፤ ኮሮጆ መገልበጥ የለም: ሕዝብ ያሻውን ይጽፋል፤ በድምጹ ይሾማል፤ በድምጹ ይሽራል: ዜጋ ይከበራል፤ ግዴታው ብቻ ሳይሆን መብቱም ይጠበቅለታል፤ በመሆኑም ሕዝቡ ለአገሩ ብልጽግናና እድገት በጋራ ተግቶ ይሠራል፤ ለፈረንሳይ ሰልጣኔም መሠረቱ ይህ ነው::*

*ሕይወት ማለት ምን ማለት እንደሆነ: ጥቂት ማለት እሻለሁ፤*
*ሕይወት ማለት፡ አቶ መለስ እንደሚሉት፡ ጥቂት ዘረኞች ወንድማማች የሆነ ሕዝብን፡ በጎሳ፤ በዘርና በሃይማኖት ከፋፍለው፡ የአገርን ሃብት እየዘረፉና እያዘርፉ ሲቀማጠሉ፡ አብዛኛው ህዝብ በረሃብ የሚረግፈበት ምድረ ገሃነም ሳይሆን፤*

*ሕይወት ማለት፡ የአንድ አገር ሕዝብ፡ እያንዳንዷን ቅጽበት: ደስታም ይሁን ሃዘን፤ ክፋም ይሁን ደግ፤ ልማትም ሆነ ጥፋት፤ ማግኘትም ሆነ ማጣት፤ አብሮ በጋራ የሚቋደሰበት፡ የፍቅር፤ የመተሳሰብ፤ የመከባበርና በእኩልነት አብሮ የማደግ፡ መንፈስና ድርጊት ነው ።*

## 9. « የፍቅርን ነገር ቢሰማ ጅብ፤

## አጥንቱን ይዞ አጀብ አጀብ »

*ጅብ ብሎ ፍቅር አዋቂ ወያኔ ብሎ በደርግ ስርአት የቀይ ሽብር ሰለባ ለሆኑ የኢህአፓ አባላት ሃውልትና መጻሕፍት ቤት ዝክር ዘካሪ!!*

*የሞቱለተን ዓልማ እየገደሉ ሟችን መዘከር፤*
*ያው እንደ ደርግ እጅን በደም መንከር:: እንላቸዋለን፤*

*የቀይ ሽብር ወንጀለኛ ሃርቃ ሃሮዬን: የፍትህ ሚኒስቴር አድርጎ የሾመ ወያኔ: በቀይ ሽብር ላለቁ ወገኖቻችን: ሃውልት አሠራሁ ብሎ መመጻደቅ: ላመኑበት ክቡር ዓላማ: የወደቁ ወንድሞቻችንና እህቶቻችንን አፅም ሠላም በመንሳት ከዘመድ አዝማዳቸው የፖለቲካ ፍጆታ ለመቃረም የተደረገ የፖለቲካ ቁማር ነው::*
*የነሱ ሃውልት በመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ልብ ውስጥ ተሠርቶ ከተመረቀ ቆይቷል::*
*በዚህ ድርጊታቸው ወያኔዎች ሆድ ብቻ እንጂ የሚያስብ ጭንቅላት እንዳልፈጠረላቸው እንረዳለን::*

*<u>መግቢያ</u>*

*ሕይወት: ብዙ ገጽ ያለው መጽሃፍን ትመስላለች፤ እያንዳንዱ ገጽ በርዕሱ፤ በቃላቱና: በዐረፍተ ነገሮቹ እንደሚገለጽ ሁሉ: እያንዳንዷ ሕይወትም: የራሷ የሆነ ምንነት፤ የራሷ መግለጫ፤ የራሷ ጉዞና የራሷ የሆነ ግብ አላት::*
*ምንም እንኳን: የራሱን ሕይወት እንድትጣፍጥ: ወይም እንድትመር አድራጊው: እራሱ ባለቤቱ ቢሆንም፤ ከሱ ቁጥጥር ውጭ በሆኑ ተፈጥሯዊ፤ ማሕበራዊ፤ መንፈሳዊና እንዲሁም ሥጋዊ: እሰጥ አገባዎች የተነሳ: አንዲት ህይወት ምህዋሯን: ወይም ፈሯን ለቃ: ባልታሰበ ቦታ፤ ባልታሰበ ጊዜና ባልተጠበቀ ሁኔታ መሆን የሚገባት ቦታ ሳትሆን ሆና ትገኛለች::*
*እናም ይችን ሕይወት ያልታደለች ሕይወት እንበላት::*

*ሌላዋ ሕይወት ደግሞ: ተፈጥሯዊ፤ ማህበራዊ፤ መንፈሳዊና ሥጋዊ እሰጥ አገባዎችን: በክህደት፤ በብልጣብልጥነትና በማስመሰል፤ በሌላም ሌላም ምክንያቶች ተፈናጣ: ባልታሰበ ጊዜና: ባልታሰበ ሁኔታ: መሆን በማይገባት ቦታ ሆና ትገኛለች::*
*ይችን ሕይወት ደግሞ ጊዜ የሰጣት ሕይወት እንበላት::*

*ባንድ መጽሐፍ ውስጥ ባሉ ሁለት ገጾች ውስጥ: የተለያየ ርዕስና ይዘት እንደሚነበብ ሁሉ፤ እነዚህ ሁለት ነፍሶችም: የየራሳቸው የሆነ የተለያየ የአኗኗር ዘዬ ይገፋሉ::*
*የሚደንቀው ግን: ሁለቱም ኑሮን እየኖርን ነው ማለታቸው ነው::*

*በሃቅ የገና ዱላ የተለጋችው ሕይወት ግቢን ስትስት፤ በጠማማው የገና ዱላ የተለጋችው፡ ባልታሰበ ጊዜና ባልታሰበ ቦታ ሆና ስትንደላቀቅ እናገኛለን፡፡*

*« ከእንጨት መርጠ ለታቦት፤*
*ከሰው መርጠ ለሹመት » ይላል ያገሬ ሰው፡፡*
*ከደን ምንጠራ የተነሳ ለታቦት የሚመረጥ እንጨት እንደጠፋ ሁሉ፤ ከሰውም ሰው የሆነ ሰው ጠፍቶ፡ አቶ መለስ ዜናዊ በምኒልክ ቤተመንግስት ሆነው፡ ምኒልክ የገነቧት ኢትዮጵያን ሲቦረቡሩ የምናይበት ዘመን ላይ ደርሰናል፡፡*

*« አንቺ ባንዲራ አምስት ዓመት ሙሉ ማተቤ ነበርሽ...........አንቺ አገር ወንድ አይፈጠርብሽ » ብሎ ነበር በላይ ዘለቀ፡፡*

*« ቃሌን ባታከብሩ ጥቁር ውሻ ውለዱ » ብለው ነበር እምዬ ምኒልክ፡፡*

*ታዲያ ለዚህ ያበቃን፤*
*የበላይ ዘለቀ ወይስ የምኒልክ እርግማን ?!*

*በመጀመሪያ ከሩሲያ በሻንጣ ተጭኖ የመጣው አብዮት ያደማንን ሰናሰበው ዝግንን ይላል፡፡*
*ኢትዮጵያ ለሰንት ዘመን ደክማ ያስተማረቻቸው ልጆቿን ባንድ ጀንበር ውሰጥ እንደ እቶን እሳት በልቶ፤ ወላጅ ያለጧሪ፤ እህት ያለወንድም፤ አባት ያለ መተኪያ፤ አገር ያለ መመኪያ አስቀረ፡፡*
*ሁለተኛናዋ አብዮት ደግሞ፤ ከአልባኒያ ተደቅላ፤ በደደቢት በረሃ ተዘርታና በቅላ፤ ትግራይን ለመገንጠል አልማ፤ ሳታሰበው አዲስ አበባ ከች ያለችው፡ የወያኔ አብዮት፡ ጭብጥ ፍሊጋ መጥታ፡ እፍኝ ሙሉ በማግኘቷ፡ መላቅጡ ጠፍቷት፡ በዘረኝነት፤ በሃይማኖትና በጎሳ ከፋፍላ እያባላችን፡ ይኸው 20 ዓመት ሞላት፡፡*
*ከአሁን በኋላስ ዲሞክራሲ ከውጪ በሻንጣ ሸክፈን ነፃ እናወጣሃለን የሚሉን ይኖሩ ይሆን ? እኛስ የሚሰማ ጆሮ፤ የሚያምን አይምሮ ይኖረናል ?*
*ወይስ ሰው ባገሩ፡ ሰው በወንዙ፡ ......ተባብለን በራሳችን ወግና ጀግንነት ለዳግም ነፃነታችን እንነሳለን?*

*የተቃራኒዎች መኖር የተፈጥሮ ሕግ ነው፤ ነጭ ባይኖር የጥቁር፤ ጨለማ ባይኖር የብርሃን፤ ሰማይ ባይኖር የምድር፤ እሳት ባይኖር የውሃ፤ ወንድ ባይኖር የሴት....ወዘተ ማንነት መገለጽ ባልተቻለ ነበር፡፡ ታዲያ አቶ መለስ፡ ይኸንን የተፈጥሮ ሕግ ይክዱና፡ ሁሉም የሳቸው ጆሌ፤ የሳቸው ፎቶ ኮፒ፤ እንዲሆን ይሻሉ፡፡ በዚህም የተነሳ፡ ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶችን፡ እንደ አፍራሽ፤ የሳቸውን ድርጅት ወያኔን፡ እንደ አገር አልሚ፡ እያደረጉ ዘወትር ያደነቁሩናል፡፡*

አቶ መለሰ በትግራይ የማሌሊት 30ኛ የምስረታ በአል ላይ፤ በማስከተልም በፓርላማ ተብያቸው፡ ያሰሙትን ንግግር ላጤነ: ወያኔን ካልደገፉ በሏቸው: የሚመስል ትዕዛዝ ሰተዋል፤ በዚህም በትግራይ የአረና ተመራጭ የነበሩት፡ አቶ አረጋዊ ገብረዮሐንስ መገደላቸው ይታወቃል ::
ቀጥሎም ለውጪ ጋዜጠኞች፡ ያደረጉትን ንግግር ላዳመጠ: ምን ያህል አስተዳድርሃለሁ የሚሉትን ሕዝብ እንደሚጠሉትና፡ እንደሚፈሩት ያሳያል :: እንግዲህ: **ከገማ እንቁላል ጫጩት አይጠበቅምና** እሳቸውም ጠልተውንና ፈርተውን፤ እኛም ሳንፈቅዳቸው እየጎረበጡንና እያቅለሸለሹን፤ አብረን ከምንኖር ለምን በወጉ አንፋታም? አይሻልም? እባብ ምንም ጸሎት ቢያበዛ፡ እርግብ መሆን አይችልም፤ ነገ የምንተነፍሰውን አየር እንኳን: በማንኪያ እየቆነጠሩ: በመስጠት፤ በነሱ መልካም ፈቃድ የሚሰጡንና የሚነሱን እንዳይሆን ያሰፈራል ::
ጎበዝ ማሽላ እንኳን እራሱን ለመቻል ነው የሚበቅለው፤ ታዲያ የሰው ልጅ እራሱን ለመቻል ከማሽላ ማነሰ አለበት??

መደምደሚያ

በወቅቱ እየተከሰተ ያለ፡ አንድ አሳሳቢ ጉዳይ፡ ዜጎች ኢፍትሃዊነትን፤ አንባ ገነንነትን፤ አድሎን፤ ዘረኝነትንና፡ ጎሰኝነትን ለመለወጥ፡ ሳያሰልሱ ከመታገል ይልቅ፡ ሃይማኖትን እንደ መጠልያ፡ ወይም መሸሸጊያ ዋሻ በማድረግ፡ እግዚአብሔር ያውቃል፡ ወይም እሱ ያመጣውን እሱ እስኪመልሰ፡ እየተባለ እጅን አጣጥፎ የበደልን ገፈት መጋት ተለምዷል ::
ይህ ትጥቅ አስፈቺና አዘናጊ ምርጫ በመሆኑ መታረም አለበት ::
ይህን በማድረግ የመከራን ቀን ከማራዘም በቀር የሚያመጣው ለውጥ የለም ::
እግዚአብሔር የሚያስብ ጭንቅላት፤ የሚሠራ እጅ፤ የሚራመድ እግር፤ የሚሰማ ጆሮና የሚያይ ዐይን ሰጠ፤ ከዚህ በላይ ምን ያድርግ? እኛው እራሳችን ለመብታችን መከበር እንሠራባቸውም፤ አንጠቀምባቸውም ካልን እሱ ምን ያድርግ?
ዳግም ወደዚህ ምድር መቶ ተወልደና ተሰቅሎ እንዲያድነን እንሻለን? ይህ እጅን አጣምሮ የማንጋጠጥ አዝማሚያ አደገኛ ከመሆኑም በላይ እግዚአብሔርንም መፈታተን ሰለሆነ መወገድ አለበት ::

ሰው ሃይማኖት አይኑረው፤ ፈጣሪውን አያምልክ፤ ማለቴ ሳይሆን፤ ሃይምኖት የመከራችን ዘመን ማራዘሚያ መሆን የለበትምና ይታሰብበት ::

ድል ለአኢትዮጵያ ሕዝብ!

እግዚአብሄር ኢትዮጵያና ሕዝቧን ይባርክ!!

ሚያዝያ 9 ቀን 2002 ዓ.ም. (April 17 2010)